# Child Care Benefit (ልጅን ለመንከባከብ ድጎማ) እና Child Care Tax Rebate (ልጅን ለመንከባከብ ከታክስ ተመላሽ)



## Child Care Benefit and the Child Care Tax Rebate—Amharic

Child Care Benefit (ልጅን ለመንከባከብ ድጎማ) ህጋዊ ፈቃድና ተቀባይነት ባለው መዋእለ ህጻናት ለልጆቻቸው እንክብካቤ ለሚጠቀሙ ወላጆች የወጪ እገዛ ያደርጋሉ። Child Care Tax Rebate (ልጅን ለመንከባከብ ከታክስ ተመላሽ) ደግሞ ለሚሰሩ ወላጆች ለልጅ እንክብካቤ ስለሚወጣ ክፍያ ይረዳል።

## Child Care Benefit (ልጅን ለመንከባከብ ድጎማ) ማግኘት የሚችለው ማነው?

የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሁሉ የሚያሟሉ ከሆነ የChild Care Benefit (ልጅን ለመንከባከብ የሚሰጥ) ድጎማ ሊያገኙ ይችላሉ።

- የሚያሳድጉት ልጅ ካለ
- ልጅዎ ህጋዊ ፈቃድና ወይም በተመሰከረለት መዋእለ ህጻናት የሚሄድ ከሆነና ወጪን መክፈል ለሚገባዎት እርሶ ከሆኑ
- ልጅዎ የሚያስፈልገውን ክትባት የወሰደ (ወይም ክትባት ከመውሰድ ነጻ የሆነ) ከሆነ
- እርሶ ሆኑ ባለቤትዎ ተገቢውን የመኖሪያ ፈቃድ የምታሟሉ (ወይም የማይመለከታችሁ) ከሆነ

Approved Child Care (**ተቀባይነት ያለው የህጻናት መዋያ**) በDepartment of Families, Community Service and Indigenous Affairs (በቤተሰብ፣ የኮምዩኒቲ አገልግሎትና በኢንዲጂነስ ጉዳይ መምሪያ) ጽ/ቤት በኩል ይቀርባል። ብዙዎቹ የቀን መዋያዎች፣ የቤተሰብ የቀን መዋያዎች፣ ከትምህርት ሰዓት በፊትና በኋላ መቆያ፣ በበዓልና የእረፍት ጊዜ፣ በቤት ውስጥና በየአጋጣሚው ሁኔታው ሲፈቅድ ለሚሰጥ አገልግሎት ፈቃድ ያገኘ የህጻናት መዋያ ነው።

Registered Child Care (**የተመዘገበ ይህጻን መዋያ**) ልጆችን ለመንከባከብ ብቃት አላቸው ተብለው በFamily Assistance Office (የቤተሰብ ጉዳይ ርዳታ ሰጪ ጽ/ቤት) በኩል የተመዘገቡ ሆኖ አያቶች፣ ዘመዶች፣ ጓደኞች ወይም ሞግዚቶች በስራ ሁኔታ የሚሰጡት አገልግሎት ነው። እንዲሁም በግል የቅድመ ት/ቤቶችና መዋእለ ህጻናትና ከትምህርት ሰዓት በፊትና በኋላ እንክብካቤ እና የአልፎ አልፎ እንክብካቤ መስጫ አገልግሎት ያካተተ ይሆናል። ለልጆች እንክብካቤ ሰጪ አገልግሎት የChild Care Benefit (ልጅን ለመንከባከብ የሚሰጥ) ለማግኘት እርሶም ሆኑ ባለቤትዎ በስራ ላይ ያሉም ሆነ በትምህርት ወይም በስልጠና ላይ ካሉ መመዘኛውን ማሟላት ይገባችኋል።

**ማግኘት የሚችሉት የሰዓት ብዛት**

የChild Care Benefit (ልጅን ለመንከባከብ ድጎማ) ማግኘት የሚገባቸው ቤተሰቦች ለእያንዳንዱ ልጅ በሳምንት 24 ሰዓት ታዋቂ በሆነና በተመዘገበ የልጅ ተንከባካቢ ሊያገኙ ይችላሉ።

- እርስዎና ባለቤትዎ በስራ ላይ ወይም ስራ በማፈላለግ ላይ ከሆናችሁ፣ በስልጠና ላይ ወይም በትምህርት ላይ ቢያንስ ቢያንስ በሳምንት 15 ሰዓት ወይም በአስራ አምስት ቀን 30 ሰዓት የምታጠፉ ከሆነ ወይም እነዚህ መመዘኛዎች የማይመለከታችሁ ከሆነ ለእያንዳንዱ ልጅ እስከ 50 ሰዓት የሚደርስ የChild Care Benefit (ልጅን ለመንከባከብ የሚሰጥ) ታዋቂ በሆነና በተመዘገበ የልጅ ተንከባካቢ አገልግሎት ልታገኙ ትችላላችሁ።
- እርስዎና ባለቤትዎ በስራ ላይ ወይም ስራ በማፈላለግ ላይ ከሆናችሁ፣ በስልጠና ላይ ወይም በትምህርት ላይ በሳምንት ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ የምታጠፉ ከሆነ ወይም እነዚህ መመዘኛዎች የማይመለከታችሁ ከሆነ ለእያንዳንዱ ልጅ እስከ 50 ሰዓት የሚደርስ የChild Care Benefit (ልጅን ለመንከባከብ የሚሰጥ) ታዋቂ በሆነና በተመዘገበ የልጅ ተንከባካቢ አገልግሎት ልታገኙ ትችላላችሁ።
- እርስዎም ሆኑ ባለቤትዎ በስራ ላይ ስለሆናችሁ፣ በስልጠና ላይ ወይም በትምህርት ላይ በመሆናችሁ የተነሳ (ወደ ስራና ወደ ቤት መጓጓዣን ጨምሮ) በሳምንት ውስጥ ከ50 ሰዓት በላይ የChild Care Benefit (ልጅን ለመንከባከብ የሚሰጥ) ታዋቂ በሆነና በተመዘገበ የልጅ ተንከባካቢ ሊያገኙ ይችላሉ።

## ለChild Care Benefit (ልጅ መንከባከብ ድጎማ) ማግኘት የምችለው ምን ያህል ነው?

ሁሉም ተመን ከሐምሌ/July 7 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።

በተመዘገበ የልጅ ተንከባካቢ የሚጠቀሙ ቤተሰቦች የዓመት ገቢያቸው $36,573 ዶላር ወይም ከፍተኛ ከሆነ ለChild Care Benefit የሚሰጠውን ከፍተኛ ክፍያ ያገኛሉ። እድሜው ለትምህርት ላልደረሰ ልጅ የሚሰጠው ከፍተኛ የChild Care Benefit ድጎማ ክፍያ በሰዓት $3.47 ዶላር ወይም $173.50 በየሳምንቱ ለሚሰጠው 50 ሰዓት ይሆናል። እድሜው ለትምህርት ለደረሰ የሚሰጠው ከፍተኛው የChild Care Benefit ድጎማ እድሜው ለትምህርት ካልደረሰው ልጅ ከመቶ 85 እጅ ብቻ ነው። እንክብካቤ ለሚደረግላቸው ልጆች ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ህጻን የክፍያ ጭማሪ ይደረጋል።

We speak your language ✆ 13 1202

www.familyassist.gov.au

Australian Government
Family Assistance Office

የቤተሰብዎ የገቢ መጠን $36,573 ዶላር ሲደርስ የChild Care Benefit ድጎማ ይቀንሳል። ከገቢ ተመን በላይ ለሚያገኙ ቤተሰቦች ምንም ዓይነት ዝቅተኛ የChild Care Benefit ድጎማ ተመን እንደማያገኙ ነው። የChild Care Benefit ድጎማ የማይከፈልበት የገቢ መጠን ለአንድ ህጻን $126,793 ዶላር፣ ለሁለት ህጻናት $131,457 ዶላር፣ ለሶስት ህጻናት $148,452 ዶላር እንዲሁም ከሶስት ህጻን በኋላ በተጨማሪ ለእያንዳንዱ ህጻን $28,020 ዶላር ይሰጣል። እነዚህ ቤተሰቦች እንደ ዜሮ የልጅ እንክብካቤ ድጎማ እንዳላቸው ተደርጎ ይታያል። ታዲያ በዚህ ምክንያት ቤተሰቦች የልጅ መንከባከቢያ እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል።

እድሜው ለትምህርት ላልደረሰ ልጅ የሚሰጠው ዝቅተኛው የChild Care Benefit ክፍያ በሰዓት $0.581 አንስቶ በየሳምንቱ 50 ሰዓት እንክብካቤ ለእያንዳንዱ ልጅ እስከ $29.05 ይደርሳል። ለትምህርት ለደረሰ ልጅ ተመን ከመቶ 85 እጅ እድሜው ለትምህርት ካልደረሰው ተመን ይሆናል። በተመዘገበ መንከባከቢያ የሚጠቀሙ ከሆነ የChild Care Tax Rebate ክፍያ እንደማያገኙ ማስተዋሉ ጠቃሚ ነው።

## የChild Care Tax Rebate ክፍያ ማግኘት የሚችለው ማን ነው?

የሚከተሉትን ሁኔታዎች ካሟሉ የChild Care Tax Benefit ክፍያ ማግኘት ይችሉ ይሆናል፡

- ተቀባይነት ባገኘ የልጅ መንከባከቢያ ከተጠቀሙ
- የChild Care Benefit ክፍያ ለማግኘት ብቁ ሆነው ሲገኙ
- እርሶና ባለቤትዎ ለሥራ፣ ለስልጠና ለትምህርትና ፈተና ብቃት ሲኖራችሁ(የድጎማ ክፍያን ለማግኘት)።

ምን ያህል የChild Care Tax Rebate ክፍያ ማግኘት እችላለሁ? ከሐምሌ/July 7 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ የተፈቀደላቸው ቤተሰቦች ከኪሳቸው ከሚከፍሉት ውስጥ ከመቶ 50 እጅ የሚሆነው የልጅ መንከባከቢያ ፍቃድ ባለው የእንክብካቤ መስጫ ወጪ ይከፈላል ይህም በዓመት ለእያንዳንዱ ህጻን ብዝቅተኛ እስከ $7,500 ዶላር ይከፈላል።

## ተጨማሪ ማብራሪያ ማግኘት ከፈለጉ፣

- የFamily Assistance Office (የቤተሰብ ጉዳይ ርዳታ ሰጪ ጽ/ቤት) በስልክ ቁጥር 13 1202 ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ8.00am እስከ 5.00pm (EST) ባለው ሰዓት ውስጥ በመደወል በአማርኛ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።
- በድረገጻችን www.familyassist.gov.au ላይ ይገኛል።
- በአቅራቢያዎ የሚገኘውን Family Assistance Office በMedicare Australia መስሪያ ቤቶች፣ በCentrelink የባለጉዳዮች አገልግሎት ማእከሎችና በታክስ ጽ/ቤቶች የመገበያያ ቦታዎች ላይ ያገኙታል።